# <u>የአማርኛ ትምህርት የፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች</u>

## <u>ክፍል አራት</u>

1. አንድ ሀረግ ምን ዓይነት ሐረግ እንደሆነ የሚወስነው በሀረጉ ውስጥ ............ ሆኖ ከሀረጉ በስተቀኝ የቀረበው ቃል በሚመደብበት የቃል ክፍል ነው ::

   ሀ) ሀረግ ለ) መሪ ሐ) አንቀጽ መ) ድርሰት

2. **<u>ጥራዝ ነጠቅ</u>** የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺ:

   ሀ) ግልብ እውቀት ያለው ለ) ጥልቅ ትምህርት የሌለው

   ሐ) ብዙ ያልተማረ መ) ሁሉም

3. **<u>ተደራሲያን</u>** የሚለው ቃል አብገር ቅጥያ የትኛው ነው ?

   ሀ) ን ለ) ኣን ሐ) ተደራሲ መ) ሲያን

4. **<u>ካህናት</u>** በዚህ ቃል ውስጥ የብዙ ቁጥር አመልካች የቱ ነው?

   ሀ) ናት ለ) ት ሐ) ካህን መ) ኣት

5. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የአንስታይ ፆታ አመልካች ቅጥያ የሆነው :

   ሀ) እት ለ) ኢት ሐ) ዋ መ) ለ እና ሐ

6. **<u>የአዞ እንባ</u>** የዚህ ፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺ:

   ሀ) የለበጣ ሃዘን ለ) እውነተኛ ሃዘን

   ሐ) መከፋት መ) ማልቀስ

7. የእሱም <u>ዳፋ</u> ለእኔም ተረፈኝ:: የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሆነው:

   ሀ) ጦስ ለ) ሱስ ሐ) ብድር መ) መልካምነት

8. የምግብ ዋጋ **<u>ንረት</u>** አሳሳቢ ሆኗል :: የተሠመረበት ቃል ፍቺ ምንድን ነው ?

   ሀ) እጥረት ለ) ውድነት ሐ) መትረፍረፍ መ) መክሰር

LIVEWORKSHEETS

9. **<u>ዶፍ</u>** ዝናብ ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ) ቀላል　　ለ) ወፍራም　　ሐ) ደረቅ　　መ) ከባድ ውይም ሀይለኛ

10. ቤቱ **<u>ወና</u>** ሆኗል ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ) ክፍት　　ለ) ሰው የበዛበት　　ሐ) ባዶ　　መ) ሙሉ

11. የአዲስ አበባ ሕይወት ነፍስ ዘርቶ **<u>መላወስ</u>** ይጀምራል ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ) መተንፈስ　　ለ) መነጋገር　　ሐ) ማስተዋል　　መ) መንቀሳቀስ

12. **<u>ሁሉም በየፊናው</u>** ወዲያ ወዲህ ይርመሰመሳል ሲል፡

ሀ) በየ አቅጣጫው ይሯሯጣል　　ለ) ሁሉም በየቦታው ያለቅሳል

ሐ) ሁሉም በያለበት ይጨፍራል　　መ) ሁሉም በየድርሻው ይለምናል

13. **<u>ረጭ</u>** ብሎ የቆየው ሲል፡

ሀ) ፀጥ ብሎ　　ለ) ሲንጫጫ የቆየው

ሐ) ሲያጉረመርም የቆየው　　መ) ሲንቀሳቀስ የቆየው

14. አበበች **<u>እጅግ መሰሪ</u>** ናት ፡፡ የተሰመረበት ሃረግ አይነት ምን ይባላል?

ሀ) ስማዊ ሃረግ　　ለ) ግሳዊ ሃረግ　　ሐ) ቅጽላዊ ሃረግ　　መ) መስተዋድዳዊ ሃረግ

15. **<u>የምድር ጉድ</u>** ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ) ምድር ላይ የበቀለ　　ለ) በጣም አጭር

ሐ) ምድር የማይችለው　　መ) ሃይለኛ

16. **<u>ፀጉር መሰንጠቅ</u>** ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ) ፀጉር በደንብ ማበጠር　　ለ) ስህተት መፈለግ

ሐ) ፀጉር መጠቅለል　　መ) ለ እና ሐ

17. ከሚከተሉት ውስጥ ስማዊ ሀረግን በመሙያነት የያዘው ዓ/ነገር የቱ ነው?

ሀ) ሙሉወርቅ ጠንካራ ተማሪ ናት　　ለ) ሳምራዊት ሳቂታ ልጅ ናት

ሐ) የሳይንስ ፈተና ቀላል ነው　　መ) ሀ እና ለ

LIVEWORKSHEETS

18. ከሚከተሉት ውስጥ በአራት ምዕላድ ሊከፋፈል የሚችለው የትኛው ነው ?

ሀ) እንደአባቶቻችን ለ) ስለወንዞችን

ሐ) ከመንደራችን መ) ጎረቤቶቻችን

19. ከሚከተሉት መካከል የተገብሮ ቃል የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ነገረ ለ) ነገረች ሐ) ተነገረ መ) ተነገሩ

ያችን ጠይም ወጣት ልቤ እንዲያ ሲወዳት፣

ትናንት በዘነበው በራሰው ወሰዳት፣

20. የዚህ ቂኔያዊ ግጥም ወርቅ ምንድን ነው ?

ሀ) በጭቃው ለ) በጨቀየው

ሐ) በራሰው መሬት መ) የራስ ፀጉሩ ከግ ንባሩ ገባ ያለ ሰው

21. **ተጓዛችሁ** በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ ባለቤት ማነው ?

ሀ) እናንተ ለ) እነርሱ ሐ) እርሱ መ) እርሳቸው

22. የቅጥያዎች ሰዋሰዋዊ አገልግሎት ምንድን ነው?

ሀ) ብዛትን መግለጽ ለ) ጾታን መግለጽ

ሐ) ባለንብረትነትን መግለጽ መ) ሁሉን

23. ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱ አመዛዛኝ /አወዳዳሪ/ድርሰት ለማፃፍ ያስችላል

ሀ) የትምህርትቤት ትውስታ ለ) የዘገባ አፃፃፍ

ሐ) የገጠርና የከተማ ህይወት መ) የጦር ሜዳ ውሎ

24. በተቃራኒ ወይም በአፍራሽ የሚነገሩ የ አረፍተ ነገር ስልት መን ይባላል?

ሀ) አዎንታዊ ለ) አሉታዊ ሐ) ትዕዛዛዊ መ) ጥያቄያዊ

25. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ በነጥበቅና በመላላት ሁለት ትርጉም የሚሰጠው ቃል የቱ ነው?

ሀ) ወሬ ለ) ንቃት ሐ) በቅሎ መ) መና

LIVEWORKSHEETS

26. **ነጩ ፈረስ** ያነከሳል። በ ዐ/ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል........... ነው።

ሀ) ገላጭ ለ) ሙያ ሐ) ተገላጭ መ) ባለቤት

27. በሀተታ ውስጥ የተነሱ አከራካሪ ሃሳቦች ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ተጠቃለው የሚቀርቡበት ክፍል ምን ይባላል?

ሀ) መግቢያ ለ) ሀተታ ሐ) መደምደሚያ መ) ርእስ

28. ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱ አመዛዛኝ /አወዳዳሪ/ድርሰት ለማፃፍ ያስችላል

ሀ) የትምህርትቤት ትውስታ ለ) የዘገባ አፃፃፍ

ሐ) የገጠርና የከተማ ህይወት መ) የጦር ሜዳ ውሎ

29. የአንድ ነጥብ (የይዘት) ሌላ ስሙ ምን ይባላል?

ሀ) ትምህተ ስላቅ ለ) አዝባር ሐ) ነቁጥ መ) ሰረዝ

30. ከሚከተሉት የውይይት መመሪያዎች አንዱ ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) የውይይቱን ርዕስና አላማ ለአድማጭ ማስተዋወቅ

ለ) በማዳመጥ ዋና ዋናውን ሃሳብ ለአድማጭ ማስተዋወቅ

ሐ) ሃሳቦችን ተቀባይነት እንዲያገኝ በቂ ምክን ያት ማቅረብ

መ) ርዕሱን መገንዘብ እና መረጃ መሰብሰብ

31. ለኃጥአን የመጣ....................................

ሀ) ፃድቃንን ይቀጣል ለ) ለፃድቃን ይተርፋል

ሐ) ፃድቃንን ይመታል መ) አይመለስም

32. የበሰበሰ....................................

ሀ) በጥም ይሮጣል ለ) ዝናብ ይወዳል

ሐ) ዝናብ አይፈራም መ) ብርድ አይፈራም

33. ውሃ ሲወስድ....................................

ሀ) እያወዛወዘ ነው ለ) ከወደላይ ነው

ሐ) ከወደታች ነው መ) እያሳሳቀ ነው

LIVEWORKSHEETS

34. ከመምህሩ ........................................

ሀ) ተማሪው በለጠ ለ) ደቀመዝሙሩ

ሐ) ይሻላል መማሩ መ) ወደቀ ደብተሩ

35. ምንም ብቀጥን ................................................

ሀ) ውሃ ነኝ ለ) ጠላ ነኝ

ሐ) ጠጅ ነኝ መ) ብርዝ ነኝ

LIVEWORKSHEETS